# ስለ UNDP ፕሮጀክት ስጋት ይገባዎታል?

## የማኅበራዊና አካባቢ ደረጃ ጥበቃ ግምገማና ለባለድርሻ አካላት ምላሽ መስጫ መንገድ

Empowered lives.
Resilient nations.

### *መግቢያ*

በተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም (UNDP) የሚደገፍ ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም በእርስዎ፣ በማኅበረሰብዎ ወይም በአካባቢ ላይ ጉዳት እንዳደረሰ ወይም ሊያደርስ እንደሚችል ከተሰማዎ የመንግሥታቱን የልማት ፕሮግራም (UNDP) የማኅበራዊና አካባቢ ደረጃ ጥበቃ ክፍል እና/ወይም ለልማት ፕሮግራሙ (UNDP) ባለድርሻ አካላት ምላሽ መስጫ በኩል ጥያቄዎን በማቅረብ ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ፡፡

*የደረጃ ጥበቃ ግምገማ* – የተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም (UNDP) ለማኅበራዊና ለአካባቢ ኃላፊነት ከመውሰዱ ጋር በተያያዙ ስጋቶች ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል

የማኅበራዊና አካባቢ ደረጃ ጥበቃ ክፍል (SECU) የተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም (UNDP) የማኅበራዊና አካባቢ ደረጃዎችን ለመጠበቅ በገባው ቃልኪዳን መሠረት ኃላፊነቱን ባለመወጣቱ በፕሮጀክቱ መጎዳታቸውን በመግለጽ ቅሬታ ያቀረቡ ማኅበረሰብና ግለሰቦችን ጥያቄዎች ያጣራል፤ እንዲሁም በግኝቱ መሠረት ደረጃ ያልተጠበቀባቸውን ጉዳዮች ለማረም ምክር ይሰጣል፡፡ ይህም ከልማት ፕሮግራሙ (UNDP) የማኅበራዊና አካባቢ ደረጃዎች በታች የተተገበሩ ፕሮጀክቶችን ይጨምራል፡፡

*የባለድርሻ አካላት ምላሽ ሰጪ – የተለያዩ አካላት ቅሬታዎችንና አለመስማማትን እንዲፈቱ ያግዛል*

የባለድርሻ አካላት ምላሽ መስጫ መንገድ (SRM) በፕሮጀክቱ የተጎዱ ባለድርሻ አካላትን፣ የልማት ፕሮግራሙ አጋሮችን (መንግሥት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና በንግድ ሥራዎች የተሰማሩ አካላትን) እንዲሁም ሌሎች የልማት ፕሮግራሙ (UNDP) ፕሮጅቶች በማኅበራዊና አካባቢ ላይ ካስከተሉት ጉዳት ጋር ተያይዞ የቀረቡ ቅሬታዎችን ወይም አለመስማማቶች በጋራ ለመፍታት የሚሠሩ አካላትን ያግዛል፡፡

### *ቅሬታ ማን ማቅረብ ይችላል?*

የልማት ፕሮግራሙ (UNDP) ድጋፍ የሚያደረግለት ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም አካባቢን ወይም ደኅንነቱን የጎዳው የመሰለው ማንኛውም ግለሰብ ወይም ማኅበረሰብ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡ ተወካዮች ለምሣሌ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በተጎጂው ማኅበረሰብ ስም ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ፡፡ ቅሬታ አቅራቢዎች SRM እና SECU ስማቸውንና ማንነታቸውን ይፋ እንዳያደርጉ መጠየቅ ይችላሉ፡፡

### *ጥያቄ የት ይቅረብ?*

እባክዎ ማንኛውንም ከማኅበራዊና አካባቢ ደረጃ ጥበቃ ጋር የተያያዘ ቅሬታና ጥያቄዎን በሚከተለው አድራሻ ይላኩ፡፡
**secuhotline@undp.org.**

ከባለድርሻ አካላት ምላሽ መስጫ መንገድ (SRM) ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች በአገር ውስጥ የልማት ፕሮግራሙ (UNDP) ቢሮዎች የሚገኝ ከሆነ ለቢሮው ያለበለዚያ በዋናው መሥሪያ ቤት ላለው SRM ቡድን በኢ-ሜይል **stakeholder.response@undp.org** ማቅረብ ይቻላል፡፡

በአገር ውስጥ የልማት ፕሮግራሙ (UNDP) ቢሮዎች መኖራቸውን የልማት ፕሮግራሙ ድረ ገጽ **www.undp.org** ላይ የሚገኘውን መረጃ ይመልከቱ፡፡

### *ጥያቄዎ ምን ማካተት አለበት?*

ጥያቄዎ የሚከተሉትን ቢያካትት ጠቃሚ ይሆናል:

- ስም፣ አድራሻ፣ ስልክ ቁጥርና ሌሎች የሚገኙበትን አድራሻዎች
- ከመነሻው በግምገማ ወቅት ጠያቂው ማንነታቸው በምስጢር እንዲያዝ መፈለጋቸውን
- ስም፣ ቦታና የልማት ፕሮግራሙ (UNDP) ፕሮጀክት መግለጫ
- በጥያቄው አቅራቢው አመለካከት ፕሮጀክቱ እንዴት ጉዳት እያደረሰ እንደሆነ ወይም ሊያደርስ እንደሚችል
- ችግሩን ለመፍታት የተደረጉ ሌሎች ጥረቶችን፣ ሌሎች ግጭቶችን የመፍታት ሁደቶችን ጨምሮ፤ አመልካቹ ስጋታቸውን ለመፍታት የወሰዱት እርምጃዎች

### *ለበለጠ መረጃ*

**www.undp.org/secu-srm**

**www.undp.org/ses**

**project.concerns@undp.org**